# እነ ፐ/ር መስፍን የሙጥኝ ያሉት የስማበለው ‹‹ትግል›› ያዋጣልን?

**ወልደብርሃን ከዓዲ-ሓቂ**

**25/02/2005ዓ.ም.**

*“ክቡር ህይወታችን የከፈልነው የማንንም ቀንበር ላንሸከም፤*

*ቀንበራችንንም በማንም ላይ ላለመጫን ነው”*

*መቐለ ሰማእታት ሃውልት ላይ የተጻፈ ህያው ጥቅስ*

* * *

*“… ህውሃት/ኢህአዴግ ለሁሉም ብሄረሰቦች ህዝቦችና ሃይማኖቶች እኩልነት እንጂ ለአንድ ድርጅት ወይም ለአንድ ብሄረሰብ ልእልና አልታገለም…በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትርነት ከህውሃት ወይም ከትግራይ መሆን አለበት ለሚል አላማ አልታገልንም… እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ኢትዮጵያ በአማራ ብሄርና በኦርቶዶክስ ሃይማት ተከታይ መገዛት አለባት ከሚሉ ወገኖች አስተሳሰብ ጋር ይዛመዳል… ይህ አስተሳሰብና አሰራር ተቀብሯል፤ አይመለስም…”*

*የህውሃቱ አንጋፋ ታጋይ አቶ ስብሐት ነጋ በቅርቡ የሰጡት አስተያየት*

* * *

“አቶ ስብሐት አማራንና ኦርቶዶክስን ቀብረነዋል አሉ”

“አማራ የሚባል ብሄር የለም” ባዩ ፐ/ር መስፍን ከላይ የተጠቀሰውን አባባል በ‹‹አሉ›› ሲያጠለሹ

* * *

## ፩. የጥላቻ ፈረሶችን የተጣባ የ‹‹አሉ››ልክፍት

እነ ፐ/ር መስፍን በተሰየሙበት የተቃውሞ ፖለቲካ ‹‹አሉ›› የምትለዋ ቃል ‹‹እውነት›› የሚለውን ቃል በመተካት አገልግሎት ላይ ከዋለች እጅግ ሰነባብታለች፡፡ በሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ተተክሎ የአብዝሃ ፓርቲ ፖለቲካና የነጻ ፕረስ ሀሁ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ባሳለፍናቸው ሃያ አንድ አመታትም እነኚህ ወገኖች ‹‹አሉ››ን እንደ ስልትም እንደ ፖለቲካ ግብም በብቸኝነት ይዘውታል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ከጽሁፎቻቸውም ሆነ ከንግግሮቻቸቸው ‹‹አሉ›› እንደ መረጃ ምንጭነት ወሳኙን ድርሻ ስትይዝ፤ አሉባልታም የፖለቲካ ፍልስፍናቸው፣ የፕሮግራማቸውና የአቋማቸው ማጠንጠኛ እስኪመስል ዘወትር ይራቀቁበታል፡፡ እንደቁምነገር ፈጥነው ለአደባባይ ያበቁታል፡፡ ከባዶ ሜዳም ይሁን ከግምት ተነስተው ራሳቸው ያናፈሱትን ‹‹አሉ›› ለአንድ ሰሙን

ራሳቸው ጉድ እየተሰኙ መላልሰው እየጮሁ ያስጮሁታል፡፡ የራሳቸውንም ጩሀት «የህዝቡ ነው» ብለው ይነጉዱበታል፤ ከሱም ተነስተው «እኛ እንዲህ ነን» ብለው ይመኩበታል፤ «ልላ» ወገን ላይም ስሞታ፣ ውንጀላና ዘለፋ ያዘንቡበታል፡፡ ምንአለፋችሁ ለታቃዋሚዎች «አሉ» ማለት ሁለመናቸውን የሚገልጽ ፍጹም ነገር ነው፡፡ አሁንም ድረስ ከዚህ አዙሪት እንዳልወጡ በዚህ ሰሙን የሚሰልቋቸው «አሉ» መራሽ የማጠልሸት ዘመቻዎች በቂ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ባለፈው አመት መገባደጃ ላይ የጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ በድንገት መታመምና መሞት ተከትሎ እኒህ ወገኖች በ«አሉ»፣ በፈጠራና በግምት እኩይ ወሬዎችን በመንዛት አዲስ ሪከርድ አስመዝግበዋል። በወቅቱ «እሰይ» ብለው ከበሮ እየደለቁ መጠነሰፊ ውዥንብርና ሟርት ከመንዛት ጀምሮ የራሳቸውን ሰብአዊ ክብር ያራከሱ አስተያየቶችን እስከመስጠት ወደኋላ አላሉም። በተለይም ኢምክኒያታዊ የጥላቻ ወሬዎችን እያናፈሱ «ኢትዮጵያ ከመለስ ሞት በኋላ ትፈርሳለች» በሚል እርግጠኝነት ሲያሟርቱ ስቅ አላላቸውም። እንዲያውም አንዳንዶቹ ሃገራቸው ስትፈርስና ወገናቸው እርስበርስ ሲባላ በቀጥታ የቴሌቭዥን ስርጭት ለማየት በጉጉት ሲጠባበቁ ተስተውለዋል።

እንዲህ ላሉት ጥቂት ግን ጯሂ ሟርተኞች በሃገር ላይ ታላቅ የክህደት ወንጀል መፈጸም እጅግ ቀላል ሁኖ ቢታያቸውም በፈጠራ የሚያናፍሷቸው የጽልመት ወሬዎች ግን ጥፋተ-ኢትዮጵያን ለማብሰር ደፋ ቀና ለሚሉት ለነ ክራይስስ ግሩፕ መሰል አጋሮቻቸው እንኳ «ሪፖርት» ማዳመቅያ ከመሆን የዘለቀ ፋይዳ አልነበራቸውም። በተለይ ደግሞ ኑሮን ለማሸነፍ በየመስኩ ደፋ ቀና የሚሉት ከ80 ሚልዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ለእውነታው ቅርብ ነበሩና ያለእረፍት በትጋት ሲሰሩ ህይወታቸው ላለፈው መሪያቸው ታላቅ ክብር ሰጥተው በአንድነት አዘኑ። ሁሉም ኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ሊባል በሚችል ሁኔታ ባለፉት 21 ዓመታት በመለስና በፓርቲያቸው በኢህአዴግ አመራር ምን ያክል ተጠቃሚ እንደነበሩ በይፋ መሰከሩ፤ የዚህንም አመራር ሌጋሲዎችና ራእዮች ለማስቀጠል በአንድነት ቆሙ። ድህነትን ዋና ጠላት ብሎ በሱ ላይ መራራ ትግል እያካሄደ ሃገሪቱን በበሳል አመራር ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረስ የቻለው ኢህአዴግም የውስጥ ህብረቱን አጠንክሮ በአንድነት ከህዝቡ እያዘነ የሃገር ሰላም ሳያስነካ ሂደቱን አስቀጥሏል። በታላቁ መሪው መለየት ሳይንገጫገጭ ህያው አላማዎቹን ቀጣይ በሚተገብርበት ጎዳና እጅግ ብዙ መለሶችንና መጠነ ሰፊ ስኬቶች ሊያሳየን ቃል ገብቶ ጉዞውን ቀጥሏል።

ኢህአዴግም የህዝቡን ስሜት ከፓርቲው ግብ ጋር አዋህዶ በህገመንግስታዊው መስመር እንደሚቀጥል በነገረን መሰረት የአመራር ክፍተቱን በሰላማዊ የመተካካት ሂደት በማሳየት የ«አሉ» ልክፍተኞች የነዟቸው ሟርቶች መሰረተቢስ መሆናቸውን በተግባር አረጋግጧል። እንዲያውም ኢትዮጵያ ውስጥ በታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ የሃገር መሪ በመታመሙም ሆነ በመሞቱም

የማይታመምና የማይሞት ስርአት እንደተተከለ በሚገባ ታየ። ይህንን የተጠራጠሩ ጥቂት ጨለምተኞች ጥያቄ በሰነዘሩበት ወቅት ከከፍተኛ የኢህአዴግ አመራሮች የተሰጠው ምላሽ እውነትነቱ በተግባር ታይቷል፡፡ የጽልመት ፖለቲካ አራማጆች ግን አሁንም አልተዋጠላቸውምና ‹‹አሉ››ን ተገን አድርገው ወደ ሌላ ዙር የማጠልሸት ዘመቻ መኳዛቸው አልቀረም።

## ፪. ፕ/ር መስፍን ‹‹በቀጥታ የቴሌቭዥን ስርጭት›› ያጡትን የጥፋት ዜና ‹‹አሉ››ን በማሰራጨት ያሳካሉን?

ኢትዮጵውያን በቅርቡ ባሳለፍነው ከባድ የሃዘን ወቅት ምንም ሳይተነፍሱ ዝም ያሉ ሁለት ቁንጮ ሰዎች ነበሩ፡፡ በጭር ሲል አልወድምና በጥልቅ ጥላቻ የሚታወቁ ቀቢጸ ተስፋዎች ሲሆኑ፤ በወቅቱ ሃገር ስትፈርስ ለማየት ቤት ዘግተው በዝምታ ሲጠባበቁ ተስተውለዋል። እኒህ ሰዎች በረባ ባልረባ ነገር ሚርትና ጥላቻ ይዘው ወዳደባባይ መውጣት የማይታክቱት ፕሬዝደንት ኢሳያስ አፈወርቂና ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም ናቸው። በመልክና ባስተሳሰብ ካላቸው መቀራረብ ቀጥሎ ሌላ ተመሳሳይነታቸውን ያረጋገጡበት አንድ አጋጣሚ  የጠቅላይ ሚንስትር ሞት ከተሰማ በኋላ ለረጅም ጊዜ ያሳዩት ያልተለመደ ዝምታቸው ነበር ማለት ይቻላል።

እርግጥ የፕሬዝደንት ኢሳያስ አፍ ከተዘጋ ከራርሟል። ባለፈው ዓመት ሰርጎ ገብ ታጣቂዎች ልከው አጸፌታውን ከተቀበሉበት ጊዜ አንስቶ ዝምታቸውን ስላስለመዱን የአሁኑንም በሚገባ እናውቀዋለን። ጎዳና ላይ የቆመ የትራፊክ መብራት ቀይ አብርቶ ቢያስቆማቸውም እንኳ ‹‹ኢትዮጵያ አሳሳቢ ደረጃ መድረሷን ያሳያል›› ብለው እየጻፉ ከሰሞታ አምዳቸው የማይጠፉት ፕ/ር መስፍን  ሁሉም ኢትዮጵያውያን በብሄራዊ ሃዘን በነበሩበት ወቅት ፍጹም ዝምታን መምረጣቸው በብዙ ወገኖች ትዝብት ፈጥሯል። ቆይቶ ግን ፕ/ሩ ጭጭ ያሉት ሃገር ስትቀወጥ ‹‹በቀጥታ ስርጭት›› ቤታቸው ሁነው ለመከታተል ከጅለው እንጂ በሌላ ምክኒያት እንዳልነበር አሳወቁን። እኒህ አዛውንት በሃዘኑ ጊዜ ‹ኢህአዴግ ሲፈረካከስ› ወይም ‹ህዝብ እርስበርስ ሲባላ›  ለማየት አድፍጠው ተጠባብቀዋል። ለ21 አመታት ስልጣንን አንዴ አራት ኪሎ ጆሊ ባር ላይ ሌላ ጊዜም ‹‹ፒያሳ ሙሃሙድ ላይ ጠብቂኝ›› ብለው ሲመኙ እንደነበሩት ሁሉ በቅርቡም ፕሮፌሰሩ እቤት ቁጭ ብለው ሃገር ስትፈርስ ለማየትና ከፍርስራሹም ባንዳች መልኩ ባቋራጭ ለማትረፍ እያሰሉ ነበር። የጠበቁት ሁሉ ሳይሆን ሲቀር ‹‹አሉ››ን ይዘው ሊሳደቡና ሊራገሙ ወዳደባባይ ወጡ። ይህንንም ጥቅምት ወር መጀመርያ በወጣችው አዲስ ታይምስ መጽሄት ላይ ከጻፉት የማጠልሸት ድርሳን በገሃድ እናያለን።

ከጽሁፋቸው እንደምንረዳው ፕ/ር መስፍን በሃዘኑ ወቅት ጥፋተ-ኢትዮጵያ ‹‹በቀጥታ ስርጭት›› ባለማየታቸው ከንክኗቸዋል። ወደ ሰሙናዊ የጥላሸት መቀቢያ ጥጋቸውም ተመልሰው በመምጣት የስማበለው ሃሰት ወሬ ይዘው እኩይ ውዥንብር ነዝተዋል። የህውሓቱ አንጋፋ ታጋይ አቶ ስብሀት ነጋ (ኣቦይ ስብሓት) በመስከረም ወር አንድ የፓልቶክ ፕሮግራም ባደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ‹‹መለስ በመሞታቸውና የጠቅላይ ሚኒስተሩ ቦታም ከህውሓት ውጭ ባለ ሰው መያዙ የህውሃትን መዳከም አያሳይም ወይ?›› የሚል ጥያቄ አቅርቦላቸው ነበር። ለዚህም አቶ ስብሃት የሰጡት በሳል አስተያየት ሃገሪቱ ያለፈችበትን ተጨባጭ ሂደት የሚያሳይ ነበር።

ባጭሩ ሲቀመጥ አቶ ስብሃት ያሉት እንዲህ ነው፡- *‹‹…ህውሓት የታገለው በኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦችና የሃይማኖቶች እኩልነት እንዲከበር ነው…በቀድሞዎቹ ስርአቶች ‹የአንድ ብሄር፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሃይማት› የሚል ጎታችና ጨቋኝ አስተሳሰብ ነበር… ህውሃት ኢህአዴግ አምርሮ በመታገል ይህንን አስተሳሰብ ቀብሯል … ህውሃት/ኢህአዴግ ለሁሉም ብሄሬሰቦች ህዝቦችና ሃይማኖቶች እኩልነት እንጂ ለአንድ ድርጅት ወይም ለአንድ ብሄረሰብ ልእልና አልታገለም…በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትርነት ከህውሃት ወይም ከትግራይ መሆን አለበት ለሚል አላማ አልታገልንም… እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ኢትዮጵያ በአማራ ብሄርና በኦርቶዶክስ ሃይማት ተከታይ መገዛት አለባት ከሚሉ ወገኖች አስተሳሰብ ጋር ይዛመዳል… ይህ አስተሳሰብና አሰራር ተቀብሯል፣ አይመለስም… እንዲያውም አሁን በተደረገው የመተካካት ሂደት የታገልንበት አላማ እውን መሆኑን ስለሚያሳይ ህውሓቶች ከማንም በላይ ደስተኞች ነን እንጂ የበላይነት አጣን ብለን የምንከፋበት ሁኔታ አይደለንም…››*

ይህ የአቦይ ስብሃት ግሩም ምላሽ ግን በጥላቻ ለታወሩ የዲያስፖራ ጽንፈኞች ከባድ ራስምታት ፈጥሮባቸው በወቅቱ ‹እየየ› አቅልጠው ነበር። በየድረገጹ ‹‹ትግሬ ገዳይ›› ባይ ፉከራዎችና ጥላቻ መራሽ ምሬቶችን ቀላቅለው መጻፍ የሚወዱት እንደነ ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም (አልማርያም) እንዲሁም ከፍልስፍናቸው የዘር ጥላቻን የሚቸልሱት እንደነ ፕ/ር መሳይ ከበደ ያሉ ሰዎች ይህንን አባባል በማጣመም ‹‹*አቶ ስብሃት አማራውን ቀብረነዋል አሉ*›› ብለው አቧራ ለመቀስቀስ ጥረው ነበር። በተለይ ደግሞ በወቅቱ ጥቂት የዲያስፖራው ጽንፈኞች ‹‹ከመለስ በኋላ ኢህአዴግ አለቀለት …ኢትዮጵያም ትፈራርሳለች…›› ለሚለው ሟርታቸው ይህንን ሀሰት መንዛት እንደ ማጀብያ ሙዚቃ ለማድረግ ሞክረው አላዛለቃቸውም። እንደተለመደው ሃሰትና ሟርታቸው ከከንቱ ምኞታቸው አለመሳካት ጋር አብሮ ተንኗል። በቅርቡ ካደፈጡበት ጎሬ የወጡት ፕ/ር መስፍን ግን ይህንን ሃሰት ወሬ በስማበለው ደርሶኛል አሉ። ከኢትዮጵያ ከ15 ሺ ማይል በላይ ርቀው የሚገኙት ጽንፈኛ መሰሎቻቸው የነዙትን ‹‹አሉ›› ፕሮፌሰር መስፍን እንደ ጥሬ ሃቅ ተቀብለው እንዲህ ሲሉ ጻፉ፡-

*«በቅርቡ አቶ ስብሐት በአደረገው ቃለ መጠይቅ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የተሾመው ወያኔ ድሮም አስቦበት ወንበሩን ከአማርኛ ተናጋሪዎችና ከኦርቶዶክስ አማኞች ለማጽዳት በተዘጋጀበት እቅድ ነበር ብሏል»።*

ከዚህም የ«አሉ» ጥቅስ ፕ/ሩ በግምት ለጥጠው ባወጡት መንታ ትርጉም አባባሉ እንደ ባለ ሁለት ስለት ሰይፍ ነው ማለታቸው ደግሞ እጅግ ያስቃል። እንደኛውና «ከፊት ለፊት የተሰነዘረው አማርኛ ተናጋሪውንና የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አማኙን ለመምተር ነው» አሉና ሁለተኛው ደግሞ «አማራንና የኦርቶዶክስ ተከታዮችን መትሮ ሲመለስ ደግሞ ሰይፉ የሚቀላው ወላይታንና ጴንጤነትን፣ ምናልባትም እስልምናን ይሆናል» በማለት ፕሮፌሰሩ ውል የሳተ የጽልመት ሃተታ አቅርበዋል። የሚገርመው ደግሞ ይህንን እጅግ የተሳሳተ ድምዳሜ በድፍረትና በእርግጠኝነት የሰጡት ፕሮፌሰር ለአባባለቸው መነሻ ምክኒያትም «አሉ» መሆኑን አልሸሸጉም። ምንጫቸውንም ሲገልጹ «ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስላም ነው የሚባል ያልተጣራ ወሬ በመስማቴ ነው» ብለውት አረፉ። ያሳያችሁ ፕ/ሩ «አሉ»ን ተገን አድርገው ያልተባለን እንደ ተባለ ከመቁጠራቸው በላይ በአንድ በኩል «አማራና ኦርቶዶክስ ተመተረ» በሌላ በኩል ደግሞ «ወላይታ፣ ጴንጤም፣ እስላምና ሌላውም ይመተራል» ይላሉ።

መቼስ የእውቀትና የትንታኔው መነሻው አሉባልታ የሆነ እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ያለ ፖለቲከኛ እንዲህ የተደነባበረውን ግምታዊ ትንታኔ ለጨለምተኛ ፍላጎቱ ሲል «እውነት ነው» ቢል አይገርምም። የሚሰማቸውና የሚያምናቸው ባይኖርም እነ ፕ/ር መስፍን በፈጠራ ወሬ የየትኛውንም ብሄርና የማንኛውንም የግለሰብ ስም ማጥፋት አይታክታቸውም። ለስልጣን ሲሉም ሃገር ማጥፋት ድረስ የሚዘልቁ እብሪተኞች ናቸውና ቢዋሹ አይደንቅም። ወደ ሃቁ ስንመጣም አቶ ስብሃት ያሉት በማንኛውም ብሄር ወይም ሃይማኖት ያነጣጠረ ሳይሆን ለሁሉም ብሄረሰቦችና ሃይማኖቶች እኩልነት ጽኑ እምነት ይዘው ከታገሉበት አላማና በተግባር ከሚታየው እውነት ጋር በቀጥታ የተዛመደ ስለመሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ስለዚህም አቶ ስብሃት የሰጡት አስተያየት ሊመሰገኑ ይገባል እንጂ ቀና አስተያየታቸው አሉባልተኞች ባጣመሙት መልኩ የሚገለጽ ትርጉም አልያዘም። የድርጅታቸው እምነትና ተግባር ነጸብራቅ ለሆነው የቃላቸውና የተግባራቸውም መመሳሰልም በጎነቱ ሁሉም ኢትዮጵያውያን አሁን በውል እያጣጣሙት በመሆኑ ይከበሩበታል እንጂ አይወቀሱበትም። ሁሉም ነገር ‹ድሮ ቀረ› እያሉ 21 አመት ሙሉ ድንኳን ጥለው የሚያለቅሱት እነ ፕ/ር መስፍንና የውጭ ጌቶቻቸው ይብላኝላቸው እንጂ ለውጡንና እውነቱን ኢትዮጵያውያን በተግባር እያጣጣምነው ነው።

ፕሮፌሰሩ የአቶ ስብሐትን አስተያየት አጣምመው ባቀረቡበት ጽሁፍ ይህንን ከሃቅ የራቀ አባባል መሰረት አድርገው አስቂኝ ተቃርኖዎችንም አስነብበውናል። በጽሁፋቸውም የአስተሳሰባቸውን እርስ

በርስ መጣረስ ና የግላቸውን ግብዝነት ከስም ማጥፋት፣ ከስሞታ፣ ከእብሪትና ከሚርት ያደበላለቀ አቅርበዋል። የፕ/ሮፌሰሩን መደነባበር የሚያሳዩ ጥቂቶቹን ልጠቁማችሁ፦

- አማራ እሚባል ብሄር የለም ብለው መጮህ የሚወዱት ፕ/ር በዚህ ጽሁፍ ባንድ በኩል ‹‹ቂል የፈጠረው አማራ የሚባል ጎሳ›› እንዳለ ተሽኮርምመው ለማመን ይሞክሩና ሰውን በሃሰት ለመወንጀል ሲሉ ደግሞ ‹‹አማራ ተመተረ››። ያሳያችሁ ፕ/ር መስፍን ያልተባለን ተባለ ከማለታቸው አልፎ የለም ያሉትን ብሄርንም የሃሰት ድምዳሜ ለመስጠት ሲሉ አለ ይሉናል። እዚህ ላይ እንደምንገነዘበው በ82 አመታቸውም እንኳ ፕ/ሮፌሰሩ አማራንም ኢትዮጵያንም አያውቁም። ይህ ደግሞ የእስካሁኑ ህይወትና ልምዳቸው እርግማን ብቻ ነበር ማለት ነው።
- ይህንን ዘንግተው ወደ መደነባበርና ወደተቃርኖ ይገቡና ‹‹ *ስብሐት ኢትዮጵያውያንን ሁሉ የሚያዛምዳቸውን ሁሉ አያይም፤ እኔ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን የሚለያያቸውን ሁሉ አላይም*›› ብለው በግብዝነት ይመጻደቃሉ። ወረድ ብለው ደግሞ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከወላይታ ብሄርና ከፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ መሆኑ እንደተከፉ በምሬት ይገልጻሉ፤ ክርስትና አስነስተው ሃይለማርያም የሚል ስም ያስሰጡትን እናቱን አልዳነችም ካለ በሌላ አይመለስምና ‹‹ያስፈራል፣ ያሰጋል›› ሲሉ ልዩነትን ለጥጠው በማጦዝ አሚርተዋል። ይህ አባባላችው ደግሞ ፕ/ሩ ወደ እውነተኛው የትምክህት መስመራቸው መልሶ የብሄረሰቦችና የእምነቶች እኩልነት ላይ ያላቸውን ያረጀ ያፈጀ አስተሳሰብ በግልጽ አራምደውበታል።
- ስለ ግለሰብ፣ ስለብሄርብሄረሰቦች፣ ስለሃይማኖቶችና ስለሃገር እንዲህ የተምታታ አሉ ላይ የተመሰረተ የሃሰት ትንተና የሰጡን ፕሮፌሰር እግረመንገዳቸውን ራሳቸውን ማግዘፍ አልዘነጉም። ድሮ ከጃንሆይና ከኮሎኔል መንግስቱ ጋር ክብር ለመጋራት *እንዲህ ብያቸው ነበር* ሲሉ ከመሪዎቹ እኩይ ስራዎች ራሳቸውን አርቀው ከበጎ ምስላቸው ለመጋራት ይሞክሩ ነበር። አሁንም ፕሮፌሰሩ አዲሱን ጠቅላይ ሚንስትር በስም ሲጠሩ በቅንፍ የኔም የክርስትና ስም ሃይለማርያም ነው ብለው በግብዝነት ክብር ለመቀልወጥ ያደረጉት ሙከራ ፈገግ ያሰኛል። ቀላል ቢመስልም የፕ/ሮፌሰሩን አሉባልታ መራሽ ድንብርብር ፍልስፍና ያሳያል፤ ብሎም ፕ/ሩ የጥፋት አውርድ ፖለቲካ ላይ ለምን ያህል ጊዜ አብረው እንደኖሩ ያስረዳል። ምንም እንኳ የኪሳራ ሃውልት ሁነው ቢቀሩም።

**፫. ‹‹አሉ››ን ተገን በማደረግ የሚካሄድ የህግ ጥሰት ያዋጣልን?**

የሆነ ሁኖ እኒህ ወገኖች እንደ ተከታታይ ድራማ ከሳምንት ሳምንት ከሚለቋቸው የፈጠራ ወሬዎች፣ ስሞታዎችና ሚርቶች እንደምንረዳው ከ‹‹አሉ›› አዙሪት መቼም ቢሆን መላቀቂያ እንደሌላቸው ነው፡፡ ብዙዎቹ የተቃውሞ ፖለቲካ ልሂቃን ያላንዳች ማመንታት የሚቀበሉትና

የጥላቻ ፈረሶቻቸውንም ኮረኩረው ሽምጥ የሚጋልቡበት ጊዜያዊ መሳርያ ቢመስልም ዞሮ ዞሮ ራሳቸውን የሚጎዱ ፈርጀ ብዙ ችግሮች እንዳሉት መረዳት አይከብድም፡፡ ይህንንም የሚያስረዱን ነገሮች ቢኖሩም ቢያንስ ሶስቱን መጥቀስ ግድ ነው፡፡

አንደኛው የችግሩ ማሳያ ተቃዋሚዎች የበሬ-ወለደ ወሬን በስማ በለው ተቀባበለው ለአንድ ሰሙን በማናፈስ አቧራ ይቀሰቅሱና ወዲያውኑ ሃሰት መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላም «እውነት ነው» ብለው እንደቅርስ ጠብቀው ያቆዩታል እንጂ አይተውትም፤ መሰረተቢስነቱን ሳይቀበሉና ስህተታቸውን ሳያርሙ «አሉ»ን በደፈናው የሙጥኝ ብለው ይንከባከቡታል፡፡ እንዲያውም እሱን ደጋግመው እያጣቀሱ ይጽፉና «የታሪክ ሰነድ» ብሎም «ለእውቀት ጠቃሚ» ብለው የሚያሞካሿቸውን መጻህፍት ያሳትማሉ፤ አሉባልታ ላይ የተመሰረቱት የጥላቻ መጻህፍቶቻቸውም ይህን ይመሰክራሉ፡፡ በአሉባልታም «ስሙ-ጥር» ለመሆንና ለማትረፍ እጅግ ይራወጣሉ፡፡ እውነትን ለመቀበልና ስህተትን ለማረም ግን ቅንጣት አይጥሩም፡፡

ሁለተኛው ማስረጃ ደግሞ እነህ ወገኖች ላለፉት ሃያ አንድ አመታት በአሉባልታ ተመስርተው ያደረጓቸው ውጤት አልባ እንቅስቃሴዎችና የተከናነቧቸው ኪሳራዎች የ«አሉ»ን ጎጂነት በተግባር ቢያረጋግጡም ከስህተታቸው ተምረው አያውቁም፡፡ ራሳቸወንም ሆነ እንወክልሃለን የሚሉትን ወገን እሚጠቅም መሰረታዊ ለውጥ የማድረግ ፈቃደኝነት የላቸውም፡፡ የፖለቲካ ስልጣን ባቋራጭ ለመጨበጥ ሚጓዙበት የጥፋት መንገድና የሚራምዱት ጨለምተኛ ግብ ከማስተካከል ይልቅ ያረጀ ያፈጀ ልማድና አመላቸውን አቅፈውና አሞካሽተው ድሮን እንደናፈቁና ዘንድሮን እንደረገሙ መቀጠል ይመርጣሉ፡፡ አመል አይላጭ እንዲሉ አሁንም ድረስ ፕሮጋራማቸው «አሉ» ላይ የተመሰረቱ ስሞታዎች፣ጥላቻዎች፣ ስም ማጥፋቶች፣ ትንኮሳዎችና የጥፋት ጥሪዎችን በማያባራና ባልተገራ መልኩ ከማራገብ ፈቀቅ አላለም፡፡ ከራሳቸውም ስህተት የማይማሩ መሆናቸውን አስረግጠውልናል፡፡ይህ ደግሞ መላልሶ እየመጣ ያው የለመዱት ኪሳራ ውስጥ የሚዘፍቃቸው የከፋው ችግር ስለመሆኑ ለማንም ግልፅ ነው፡፡

ሶስተኛውና የከፋው ችግር እነዚህ ወገኖች « አሉ»ን አጥብቀው ከመውደዳቸው የተነሳ ሳይታክቱ የተጠመዱበት የማጠልሸት ፖለቲካ በስልትም ሆነ በግብ ከአፍራሽ እንቅስቃስዎችና ከልዩ ልዩ የወንጀል ድርጊቶች ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በሕግ ተጠያቂነት ማስከተሉ አይቀርም፡፡ በተለይም እነዚህ ወገኖች አሉን ተንተርሰው በሚነዟቸው ጽሁፎች ብዙ የሕግ ጥሰቶች ይፈጽማሉ፡፡ በፈጠራ ግለሰቦችን ስም ማጥፋትና ማጠልሸት የእለት-ተእለት ስራቸው ነው። ትረካቸው በእምነት ባስተሳሰብና በማንነት ከነሱ የሚለይ ወገንን ዜግነት ነጥቆ እንደባዕድ ሃይል ማንቋሸሽና መኮነን ላይ የተመሰረተ ነው። ለግል ህይወታቸውና ለሀገራቸው መሻሻል ሲሉ በቀናነት ልዩ ልዩ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ዜጎችን በሙሉ «ሎሌ» ብለው ያበሻቅጣሉ፤ ለሰላምና ለልማት ማንኛውንም ጥረት

የሚያደረጉ ወገኖችን በሙሉ ስም እያጠለሹ ለማሸማቀቅ ይጣጣራሉ፡፡ አንድ ወገን በሌላ ወገን፣ አንድ ሃይማኖት ከሌላው ሃይማኖት ወይም አንድ ብሄር ከሌላ ብሄር ለማጋጨት ውዥንብር እየነዙ፤ ብሎም ብሄሮችንና ህዝቦችን በመንግስት ላይ ለዓመጽ ድርጊት እየቀሰቀሱ ለጥፋት እያነሳሱ መንቀሳቀስ አያስጨንቃቸውም፡፡ ለባእዳንና ለለየላቸው አሸባሪ ሃይሎች በምንደኝነት በመሰለፍ የሃገር ምስል ለማበላሸት፣ ሃገር ጥቅም ለመጉዳትና ሃገር ለማፍረስ እየተራወጡም ራሳቸውን እንደ ‹‹ሃገር ወዳዶች›› ሲቆጥሩ አያሳፍራቸውም፡፡

ባጭሩ ሲገለጽ እነ ፕ/ር መስፍን የፈጠራ ወሬ በመንዛት ሕገመንግስታዊውን ስርአት ለመናድና ስልጣን ባቋራጭ ለመያዝ ሲሉ ዘወትር የተጠመዱባቸው አፍራሽ እንቅስቃስዎች ከተራ ወንጀል እስከ ሃገር ክህደት የዘለቁ የሕግ ጥሰቶች ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ እውነታን ሳይቀበሉና ስህተታቸውን ሳያርሙ አሁንም ተኩራርተው እነዚህን በመሳሰሉ የወንጀል ድርጊቶች ላይ ተጥደው እናገኛቸዋለን። እኒህ አፍቃሬ ‹‹አሉ›› ወገኖች ከተጠያቂነት የማያመልጡበትን የ‹‹አሉ›› ፖለቲካ የሙጥኝ ማለታቸው አመል ወይም ምርጫ ሆኖባቸው ቢሆንም እንኳ እንደማያዋጣቸው ለራሳቸውም ጭምር ግልጽ ይመስለኛል፡፡ ፕ/ር መስፍንም ሆኑ የስሞታ አጋሮቻቸው በስማበለው እየተመሩ በኢትዮጵያውያን መካከል ጥላቻ የሚዘሩና ጥፋት የሚጠሩ የጥላቻ ፈረሶች መሆናቸው በሚገባ ይታወቃል፤ ጽሁፎቻቸውና ድርጊቶቻቸውም ይህንን ይመሰክራሉ። ራሳቸው በሃሰት እያሞካሹ ወይም ሌላውን እየኮነኑ ሊያደናግሩ ቢጥሩም ‹‹አሉ››ን በመንዛት እያሚረቱ ሃገራችን ላይ ጥፋት ለማዝነብ የሚያደርጓቸው ጥረቶች በማንኛውም ጤናማ ህብረተሰብ በዝምታ የሚታለፉ አይመስለኝም።